# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# ህብረት ስራ ኤጀንሲ
# የሸማቾች ህብረትስራ ማህበራት
# የሥነ-ምግባር መመሪያ

**መመሪያ ቁጥር** 102/2014

# መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ  የህብረት ስራ ማህበራትን በማደራጀት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮችን መፍታት እንዲችሉ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ አንዱ ደግሞ የሸማች ህብረትስራማህበር ነው፡፡ይህ የሸማች ህብረት ስራ ማህበር የበለጠ ተጠናክሮ መስራት እንዲችል መመሪያውን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የአባላትን ተጠቃሚነት ማጉላት እንዲቻል የአመራሮች፣ስራ አስኪያጆች፣አስተዳደር ሠራተኞችናሌሎች ቅጥር ሰራተኞችበሥነ ምግባር የታነጹ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ስለሆነም የስነ-ምግባር መመሪያ በማዘጋጀት በየደረጃው የሚገኙ  የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ አካላትንየግልጽነትና የተጠያቂነት ባህልን በማዳበር አድልዎ የሌለበት መልካም አሰተዳደር እንዲኖራቸውናይህን የስነ -ምግባር መመሪያ መሰረት ያደረገ እርምት መውሰድ እንዲቻል መመሪያው ተዘጋጅቷል፡፡ስለሆነም ይህ መመሪያ ውጤታማ መሆን እንደዲችል የሥራ አመራር ኮሚቴ እንዲሁም ሠራተኞች የተሰጣቸዉን ኃላፊነት በጥሩ ሥነምግባርእንዲሰሩና ዉጤት ማምጣት እንዲችሉ ማድረግ ይጠበቃል፡፡በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ህብረት ስራ ኤጀንሲ በደንብ ቁጥር 85/2009 አንቀጽ 16 መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 2. የስነ-ምግባር መመሪያው አስፈላጊነት

1.1. በሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት የሚሰሩ ሰራተኞች እና የሥራ ኃላፊዎች ስራቸውን ሲያከናውኑ የመልካም ስነምግባር እሴቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ፣ ወጥየሆነ ተመሳሳይ የስነ-ምግባርመመሪያ እንዲኖራቸው በማስፈለጉ፣

1.2. የስነ-ምግባርመመሪያ የመልካም አስተዳደር ማስፈፀሚያ እሴቶች የሆኑትን የቅንንት፣ የታማኝነት፣ የግልፅነት፣ ተጠያቂነት እና መሰል መርሆዎችን በሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ለማስፈን ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ፣

1.3. በሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ሠራተኞችእና ኃላፊዎች የዕለት ከዕለት ተግባራቸውን ሲያከናውኑ የመልካምስነ-ምግባር እሴቶችን መሰረት በማድረግ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአመርቂ ሁኔታ እንዲወጡ የስነምግባር መመሪያ ጠቀሜታው ከፍተኛ በመሆኑ፤

1.4. በሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ የሚሰሩ አመራሮችና ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች የስነምግባር ግድፈቶችተፈፅመውሲገኙ ተመጣጣኝ የእርምት እርምጃዎች መውሰድ የሚችልበትስርአትንማጠናከርበማስፈለጉ፤

## ክፍልአንድ፡- ጠቅላላድንጋጌ

### አንቀጽ1.አጭር ርእስ

ይህ የስነ- ምግባርመመሪያ“ የአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ስራ ለሚተዳደሩ የሸማችሠራተኞች እና የሥራ አመራር የስነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 102/2014” ተብሎሊጠቀስይችላል፡፡

### አንቀጽ2 ትርጓሜ

የቃሉአገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. ‹‹ኤጀንሲ››ማለት የአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ነው፡፡
2. ‘የሸማች ህብረት ስራ ማህበር’ ማለት ሰዎች ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ፍላጎቶቻቸውን አባላት በተናጠል ሊወጡዋቸው የማይችሉዋቸውንኢኮኖሚያዊችግሮች በጋራ ለመፍታት የሚችሉበት ራሱን የቻለ ህጋዊ ሰውነት ያለው የህብረት ስራ ማህበር ነው፡፡
3. ‘ኮሚሽን’ ማለት የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማለት ነዉ ፡
4. ‘ሠራተኛ’ ማለት በኤጀንሲው ስር በሚተዳደሩ የሸማቾች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር ኮሚቴ በገቡት ውል መሰረት የዕለት-ተዕለት ስራዎችን እንዲያካሂድ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግኑኝነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡
5. አመራርማለት የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ የሥራ አመራር ወይምዩኒየን በሆነ ጊዜ ቦርድ ማለት ነዉ፡፡
6. ‘የሥራ ኃላፊ’ ማለት የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ስራ አስኪያጅ ማለት ነዉ ፡፡
7. ‹ የሥራ አመራር ኮሚቴ› ማለት በምርጫ የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራትን የሚመሩ አባላት ስብስበን ይመለከታል፡፡
8. ‘የሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል ማለት በኤጀንሲው የስነምግባር ሁኔታን የሚከታተል፣ የሚያስተባብርና የሚያማክር አካል ነዉ፡፡
9. ‘የሥነ ምግባር መኮንን’ማለት በሚንስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 144/2000አንቀጽ 7/3/ መሰረት የተቀጠረ የሥነምግባር ባለሙያ ነዉ፡፡
10. ‘ቤተሰብ’ ማለት የሠራተኛዉ ሚስት/ባል እና በሠራተኛዉ እርዳታ የሚተዳደሩ ልጆቹ እና ሌላ ሰዉ ነዉ፡፡
11. የቅርብ ዘመድ’ ማለት የተመራጭ ወይም የሰራተኛ ወላጆችን ተዋላጆችን እህቶችን ወንድሞችን እና ሌሎች እስከ ሶስተኛ ደረጃ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸዉ ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡
12. ‘ሀብት’ ማለት ማንኛዉም የማይንቀሳቀስ ወይም የሚንቀሳቀስ ወይም ግዙፍነት ያለዉ ወይም የሌለዉ ንብረት ሲሆን የመሬት ይዞታና ዕዳን ይጨምራል።
13. ‘ገቢ’ ማለት የቀን ገቢ ወይም የወር ገቢ ተብሎ ይጠራል፡፡
14. ‘የጥቅም ግጭት’ ማለት የአንድ ሠራተኛ የፋይናንስወይምሌላ አይነት ጥቅም ከመደበኛ ስራዉ ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጋጭ ወይም ግጭት ሊፈጥር የሚችል መሆኑ በበቂ ሁኔታ የሚታመን ጉዳይ ነዉ።

15. 'ሀብትን ማሳወቅ'ማለት የሠራተኛዉ ወይም የቤተሰበቡ የፋይናንስ ወይም ሌላ አይነት ጥቅም በሥራዉ ላይ ተጽዕኖ ሊያደርግ ይችላል ወይም ያደርጋል ተብሎ የሚገመት ሀብትን ነዉ፡፡
16. 'ጥቅምን ማስመዝገብ' ማለት የሰራተኛዉንና የቤተሰቡን የፋይናንስ ጥቅሞችንና ሌሎች ሀብቶችን በጽሁፍ አቅርቦ ማስመዝገብ ነዉ፡፡
17. 'ስጦታ' ማለት በሰራተኝነቱ ምክንያት ለሠራተኛዉ የተሰጠዉ ዋጋ ወይም የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያለዉ ነገር ነዉ፡፡
18. 'መስተንግዶ'ማለት በሰራተኝነቱ ምክንያት ለሠራተኛዉ የተደረገለት ነጻ የሆነ የምግብ፣ የመጓጓዣ፣ የሆቴል ወይም ሌላ የመዝናኛ አገልግሎት ነዉ፡፡
19. 'ተገቢ ያልሆነ ባህሪ'ማለት ከአሰራር የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ደንብ እንዲሁም ተቀባይነት ካለዉ ልማዳዊ አሰራር ጋር የማይጣጣም ማናቸዉም ባህሪ ነዉ፡፡
20. 'የሥነ ምግባር ብልሹነት' ማለት በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተጠቀሱት የሥነምግባር መርሆችን ወይም እሴቶችን የሚቃረን ባህሪ ነዉ፡፡
21. 'ጥቆማ ማቅረብ' ማለት በህብረት ስራ ማህበሩየሚፈጸም ተገቢ ያልሆነ አሰራርን ወይም የስነምግባር ብልሹነትን በሚመለከት የሚቀርብ መረጃ ነዉ፡፡
22. 'ሰዉ' ማለት የተፈጥሮ ሰዉ በሕግ የሰዉነት መብት የተሰጠዉ አካል ማለት ነዉ፡፡

**አንቀጽ 3 የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ የሥነ ምግባር መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባሉ **በመሠረታዊ የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ዩኒየን እና ፌዴሬሽን ያሉ የስራ አመራር እና ሠራተኞች ላይ** ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፤

**አንቀጽ 4 የጾታ አገላለጽ**

በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸዉ የሴትንም ጾታ ያጠቃልላል፡፡

**አንቀጽ 5 የስነ- ምግባር መመሪያ ዓላማዎች**

የሸማች ህብረት ስራ ማህበራት ፡-

1. የግልፅነትና የተጠያቂነት ባህልን በማዳበር የመልካም አስተዳደር ግንባታን ማጠናከር፣
2. የህዝብ አገልጋይነት ባህልን በማዳበር ለተገልጋዩች ፍትሃዊ የአገልግሎት አሰራርን ማጠናከር፣
3. ሠራተኞች እና የሥራ አመራር /ቦርድ/ ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን የሚፀየፉ እና የሚዋጉ በመልካም በስነ-ምግባር የታነፁ እንዲሆኑ ማስቻል፣
4. ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች ስራቸውን ሲያከናውኑ እና ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ከእያንዳንዱ የሃገሪቱን እና የማህበራትን የስነምግባር እሴቶች የሚጠበቁ ዝርዝር ባህሪያትን የተላበሱ እንዲሆኑ ማስቻል፣
5. የማህበራትን ሀብትና ንብረት ተንከባክቦና ጠብቆ ለባለቤቱ ማድረስ ወይም ማስረከብ እንዲቻል ለማድረግ፤

6. ሠራተኞችና ስራ አስኪያጅ መካከል የተቀናጀ አሠራር ኅልብቶ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትና መልካም አስተዳደርን ማስፈን፤ ህብትን በማስመዝገብ በሀቀኝነት መስራት
7. ፍትሐዊና ፈጣን የልማት ሚና እንዲወጡ አቅጣጫ ለማስያዝ ፤
8. የስነ- የምግባር ግድፈቶች ተፈፅመው ሲገኙ ተመጣጣኝ የእርምት እርምጃዎች ለመውሰድ የሚያስችል ስርዓቶችን ማሳየት፣ የሚሉት ናቸው።

## አንቀጽ 6 ኃላፊነት

1. ይህን መመሪያ በተለያዩ የኃላፊነት ደረጃ የሚገኙ የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ስራ አመራር ኮሚቴ ይህን የሥነ ምግባር መመሪያ በሚገባ አዉቀዉ በስራቸው ያሉት ሠራተኞች በሙሉ እንዲያውቁትና ተግባራዊ እንዲደርጉት የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው።
2. የስነ-ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል የመመሪያ አፈፃፀም በሚመለከት ለማህበራት ሠራተኞች እና የበላይ አመራሮች እንዲሰርፅ የማድረግ እና በማህበራት ውስጥ መልካም ስነ-ምግባር እንዲሰፍን አስፈላጊውን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅባቸዋል።
3. የማህበራት ሠራተኞች እና ኃላፊዎች ይህንን መመሪያ የመፈፀም ግዴታ አለባቸው።
4. የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ አመራሮች እና ሠራተኞች በመ/ቤቱ ዉስጥ ከሥነ ምግባር ጥሰት ሙስናና ብልሹ አሠራር ጋር የተያያዙ ድርጊቶች ሲፈጸሙ ለሥነ ምግባር መከታተያ ክፍል፣ ወይም ጉዳዩ ከበድ ባለ ጊዜ ለአዲስ አበባ ህብረትስራ ኤጀንሲ የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸዉ፡፡
5. 6.5 የሥነ ምግባር መኮንኑ በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተመለከቱት የስነ ምግባር መርሆዎችን አፈጻጸም በሚመለከት የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ አመራሮች፣ የሥራ መሪዎችና ሠራተኞችን የማማከር ፤የማስተማር በየሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ስላለዉ መልካም የሥነ ምግባር ሁኔታ በየጊዜዉ ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

# ክፍል ሁለት

# አጠቃላይ የሥነ ምግባር መርሆዎችና የዲስፕሊን ጥፋቶች

## አንቀጽ7 ቅንነት

**መርህ፡- ጽኑ አቋም፣ የተሟላ ስብዕና፣ የገቡትን የሙያ እና የስራ ቃል ኪዳን ማክበርን፣ በራስ መተማመን እና የላቀ የሞራል ባህሪያትን መላበስ፣**

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. የተጣለባቸዉንአደራ በሸማች ህብረት ስራ ማህበራቱ ላይ እምነት እንዲኖረዉ ሊያደርግ በሚችል መልኩ መምራት፣

2. መልካም ሥነ ምግባር በማሳየት ሥራቸዉን በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

3. ከሕግ ዉጭ ከመሥራት ፤ ተገቢ ካልሆነ አድራጎትና ከሥነ ምግባር ብልሹነት መቆጠብ፡

4. በማህበራዊና በግል ሕይወታቸው ባላቸው ተቀባይነትአባላቱ በህብረት ስራ ማህበራቱ ላይ ያለዉን አመኔታና አክብሮት ሊያስጠብቅ ወይም ሊያጎለብት በሚችል መልኩ በመምራት የህብረት ስራ ማህበሩን ዝናና ክብር ማስጠበቅ፣

**በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡**

ሀ/ የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩን ዝና የሚጎዳ ወይምሕዝቡ በህብረት ስራ ማህበሩ ላይ የሚኖረዉን እምነት ዝቅ የሚያደርግ ባህሪ ማሳየት ወይም ተግባር መፈጸም፤

ለ/ አቅሙ እየፈቀደ በሥራዉ ላይ ተገቢዉን ጥረት አለማድረግ፤

ሐ/ ሱስ በሚያሲዝ መድሐኒት ወይም በአደንዛዥ ዕጽ ሱስ በመመረዝ ወይም በልማዳዊ መጠጥ ተጽዕኖ ምክንያት ሥራን ማከናወን አለመቻል ወይም በሥራ ላይ በደል ማድረስ፤

መ/ የሥራ ባልደረባን ወይም ባለጉዳይን በጾታዊ ትንኮሳማስጨነቅ  ወይም መሞከር ወይም ለሌሎች ሰዎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፤

ሠ/  ሥራን ሙያዉ በሚጠይቀዉ የሥነ ምግባር ደረጃ አለማከናወን ፤

ረ/  ከሥራ ባልደረባቸዉ ጋር በመግባባት መሥራት ባለመቻል በሥራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን፣

## አንቀጽ8 ታማኝነት

መርህ፡-የገቡትን የሙያ እና የስራ ቃል ኪዳን መጠበቅ፣ ለማህበር አባላት፣ ለህብረተሰብ፣ ለሃገሪቱ ህጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ለስራ ባልደርቦች፣ ወዘተ.. ታማኝመሆን፣

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. ለሕገ-መንግስት ታማኝ መሆን፣
2. ለሸማች ህብረት ስራማህበሩ ህግና መመሪያ መገዛት፣
3. ሥራቸዉን ሕግንና ድርጅቱ የሚያወጣዉን መመሪያ መሠረት በማድረግ የሚጠበቅ ኃላፊነት ማከናወን ይኖርባቸዋል ፤የመንግስት ንብረት እና ሥራ ሰዓት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል፤
4. የሥራ ባልደረቦቻቸዉን ሕገ ወጥ ድርጊት ለቅርብ ኃላፊያቸዉ ማሳወቅ፣
5. የህብረት ስራ ማህበሩን ገንዘብ ንብረትና የሥራ ሰዓት ለግል ጥቅማቸዉ አለማዋል፣

በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡

ሀ/ ለተመሳሰይ ሥራ የተመደብን የሥራ ባልደረባን ጥፋት እያወቀ ለቅርብ የሥራ ኃላፊዉ አለማሳወቅ፤

ለ/ አንድ ሥራ እንዳይሠራ ወይም ዉሳኔ እንዳይፈጸም እንቅፋት መፍጠር ወይም ሥራ እንዳይሠራ ከሚያዉኩ ሰዎች ጋር መተባበር

መ/ በመንግስት የፖሊሲ ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መረጃ ሆን ብሎ መግለጽ ፤

ሠ/ በሕግ አግባብ ፍቃድ ከተሰጣቸዉ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ዉጭ ወይም ከሚመለከታቸዉ ኃላፊዎች ፈቃድ ዉጪ በሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ አገልግሎት ወይም ንብረት ወይም ገንዘብ ያለአግባብ መጠቀም ወይም ሌሎች እንዲጠቀሙ ማድረግ ወይም ለግል ጥቅም ማዋል፤

ረ/ ያለበቂ ምክንያት በሥራ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ለሚመለከተዉ አመራር ወይም አካል በወቅቱ አለማሳወቅ፤

ሰ/ በየሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ንብረትና ሀብት ላይ የስርቆት ወይም የእምነት ማጉደል ድርጊት መፈጸም፤

ሸ/ በሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ንብረት ላይ ሆንብሎ ጉዳት ማድረስ፤

ቀ/በሸማች ህብረት ስራ ማህበሩላይ ባለማወቅ ጉዳት ማድረስ፤

**አንቀጸ 9 <u>ግልጽነት</u>**

***መርህ፡-*** *አሰራሮችን እና የሚሰጡ አገልግሎቶችን፣ እንዲሁም የሃብት አጠቃቀምን፣ ሌሎች መመሪያዎችን ለተገልጋዩ እና ለማህበር አባላት በሚቻለው መንገድ ሁሉ ግልፅ ማድረግ እና መረጃ መስጠት፣*

*ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር*

1. *በአሠራራቸዉ ግልጽ መሆን እና ህብረተሰቡ ሊያዉቀዉ የሚገባንና በምስጢር ያልተያዘ መረጃ መስጠት፣*
2. *በምስጢር ሊጠበቅ የሚገባ ነው ተብሎ በሕግ ወይም በበላይ የሥራ አመራር ዉሳኔ ያልተሰጠበትን መረጃ ለሚፈልገው አካል መስጠት፣*
3. *ለሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎች እና አገልግሎቶች ግልጽ መሆንና ዉሳኔያቸዉን ወይም የሚሰጡትን አገልግሎት አስመልክቶ ከተጠቃሚዉ ጥያቄ ሲቀርብላቸዉ መረጃዉ በምስጢር የሚጠበቅ ካልሆነ በቀር ሕግና መመሪያን ተከትለዉ ተገቢዉን ማብራሪያ ወይም ምላሽ መሰጠት፣*

***በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል***

*ሀ/ ሕጋዊ ለሆነ ጥያቄ በእጁ የሚገኘዉን መረጃና ለሕዝብ ግልጽ እንዳይደረግ ያልተከለከለ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፤*

*ለ/ ለግምገማ የሚያስፈልግ መረጃ አግባብ ባለዉ አካል ሲጠየቅ በወቅቱ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፤*

*ሐ/ ባጅ አለማድረግ*

**አንቀጽ 10 <u>ሚስጥር መጠበቅ</u>**

***መርህ፡-ምስጢራዊ እና እንዲገለፁ/ እንዲወጡ ያልተፈቀዱ የግል፣ የሥራ እና የመንግሥት መረጃዎችን በሚመለከታቸው አካላት ሳይፈቀዱ ይፋ አለማድረግ፣***

*ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ማህበር* ***ሠራተኞች እና የሥራ አመራር***

1. *በሥራቸዉ ምክንያት ያወቋቸዉን ምስጢራዊ መረጃዎች መጠበቅ ምስጢራዊ ያልሆነ ወይም የማህበሩ አባላት የሚያዉቀዉን ወይም ሊያዉቁ የሚገባዉን መረጃ መግለጽ ይችላሉ፡፡*
2. *ሥራ ከለቀቁ ፣ከተዘዋወሩ ወይም በሰራም ቢሆን በራሳቸዉ ምክንያት ያወቃቸዉን ሚስጥራዊ መረጃዎች የመጠበቅ ግዴታ አለባቸዉ፡፡ጥፋትን ለማጋለጥ ለሚመለከተዉ አካል ምስጢራዊ መረጃም ማሳወቅ እንደ ምስጢር ማባከን አይቆጠርም ፡፡*

***በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል***

ሀ/ ያልተፈቀደዉን ወይም ምስጢራዊ መረጃን በማናቸዉም ሁኔታ ሆነብሎ መግለጽ፤

ለ/ ያልተፈቀደዉን ወይም ምስጢራዊ መረጃን በማናቸዉም ሁኔታ በቸልተኝነት መግለጽ፤

ሐ/ ምስጢራዊ መረጃን ለግል ጥቅም ማዋል፣

መ/ በሸማች ህብረት ስራ አሠራር ወይም በተገልጋይ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መረጃ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ሆነብሎ መግለጽ፣

**አንቀጽ 11 <u>ሐቀኝነት</u>**

**መርህ፡-እውነተኛ መሆን፣ ከማታለል፣ ሌሎችን ከማሳሳት፣ ከማጭበርበር፣ ከሙስና የፀዱ እና በሃቅ እና በፍትህ ላይ መመስረት፣**

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. በሸማች ህብረት ስራ ማህበሩበሥራቸዉ አጋጣሚ የገቡትን ቃል መጠበቅና ማክበር፣
2. ከሙስና ከማታለልና በሥልጣን አለአግባብ ከመጠቀም መቆጠብ፣
3. ለሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ማደግ የሚጠቅም ካልሆነ በስተቀር በግለሰብ ደረጃ ከሥራቸዉ ጋር በተያያዘ ማንኛዉንም ዓይነት ስጦታ ወይም መስተንግዶ አለቀበል፣

**በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡**

ሀ/ በማጭበርበር ፤በስልጣን መነገድ ፤በስልጣን አለአግባብ ሠነድ መደለዝ ወይም የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ አርማና ማህተም ለሕገ ወጥ ድርጊት መጠቀም አታላይነት ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠዉ መጠየቅ ፤

ለ/ ሐሰተኛ ወይም ተገቢ ያልሆነ የአበል ክፍያ ጥያቄ ማቅረብ

**አንቀጽ 12<u>ተጠያቂነት</u>**

**መርህ፡-ለሚሰጡ ውሳኔዎችና ለሚወሰዱ እርምጃዎች በኃላፊነት የመጠየቅ እና መልስ የሚሰጥበት አሰራርን/ሥርዓትን ማክበር፣**

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. ለሚሰጣቸዉ ዉሳኔዎችና ለሚያከናዉናቸዉ ተግባራት ተገቢዉን ምክንያት መስጠት፣
2. የህብረት ስራ ዓላማና መርሆዎችን መፈጸም፣
3. ሥራቸዉን በአግባቡ ስለማከናዉናቸዉ ኃላፊነታቸዉን ስለመወጣታቸዉ አስፈላጊዉን ማብራሪያ መስጠት፣

**በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል**

ሀ/ ስለአከናወናቸዉ ሥራዎች ለሚመለከተዉ አካል በወቅቱ ሪፖርት አለማቅረብ

ለ/ ስለአከናወናቸዉ ሥራዎች ለሚመለከተዉ አካል ሆነ ብሎ የሚያሳስት ወይም ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅረብ

ሐ/ ስለአከናወናቸዉ ሥራዎች ለሚመለከተዉ አካል በቸልተኝነት የሚያሳስት ወይም ትክክል ያልሆነ ሪፖርት ማቅረብ

መ/ የተሰጠዉን ሥራ ያለበቂ ምክንያት በወቅቱ አለማከናወን ፤

ሠ/ ያለፈቃድ ወይም ሥልጣን ሳይኖረዉ በኮምፒዉተር የተያዘ ዳታን ማጥፋት ወይም መለወጥ ወይም የተሳሳተ መረጃ ማስገባት ፤

ረ/ ኃላፊነት ያለበት ከሥራዉ ጋር ተያያዥነት ያላቸዉ መረጃዎችን ሲጠየቅ ያለበቂ ምክንያት ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በወቅቱ አለመስጠት ፤

**አንቀጽ** 13 <u>**የአባላትን ጥቅም ማስቀደም**</u>

**መርህ፡-** የሚሰጡ አገልግሎቶች እና በስራ ላይ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የማህበር አባላት እና የሕብረተሰብ ፍላጎት እና የሃገርን ጥቅም ማስጠበቅ መርህን መሠረት ማድረግ፣

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ **ሠራተኞች እና የሥራ አመራር**

1. የግል ጥቅማቸዉን የቤተሰቦቻቸዉን የሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም ቡድን ሳይሆን የሕብረተሰቡን ጥቅም መሰረት በማድረግ ስራቸዉን ማከናወን፣
2. በሕግ ግዴታ ያለባቸዉ የራሳቸውን የገንዘብ ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ፣
3. ከመደበኛ ሥራቸዉ ጋር ሊጋጭ የሚችል ማንኛዉም ዓይነት ጥቅም ማሳወቅ እንዲሁም ግጭቱን ማስወገድ፣

**በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል**

ሀ/ የግል ወይም የተወሰኑ ቡድኖችን ጥቅም ከሕብረተሰቡ ጥቅም ማስቀደም፡፡

ለ/ በሕግ ግዴታ ያለበት ጥቅምን ሆነብሎ አለማሳወቅ

ሐ/ በሕግ ግዴታ ያለበት ጥቅምን በቸልተኝነት አለማሳወቅ፤

መ/ በሕግ ግዴታ ያለበት የራሱንና የቤተሰቡን ሀብት ለማስመዝገብ ፈቃደኛ አለመሆን፤

**አንቀጽ** 14 <u>**ሕጋዊ በሆነ ሥልጣን መገልገል**</u>

**መርህ፡-**የተሰጠን ስልጣንና ኃላፊነት ከታሰበለት ዓላማ ውጪ ለራስ ወይም ለሌሎች በሚመች እንዲሁም ሌሎችን በሚጎዳ መልኩ አለመገልገል ወይም አለማዋል፣

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. ሕብረተሰቡን በአግባቡ እንዲያገለግሉና ኃላፊነታቸዉን እንዲወጡ የተሰጣቸዉን ሥልጣንና ኃላፊነት ለድርጅቱ በሕግ ተወስኖ በተሰጠዉ የሥልጣን ገደብ ዉስጥ መጠቀም፣
2. የህብረት ስራ ማህበሩን አዋጅን ደንብን ወይም መመሪያን መሠረት በማድረግ ሥራቸዉን ማከናወን፣
3. በሥልጣናቸዉ ያለአግባብ መገልገል የለባቸዉም ሥልጣናቸዉን የግል ጥቅም ለማግኘት አለማዋል፣

**በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል**

ሀ/ ከሥልጣን በላይ መሥራት ወይም በሥልጣን አለአግባብ መገልገል ወይም በሥልጣን መነገድ ወይም በወንጀል ሕጉ ላይ የተቀመጡትን ተመሳሳይ ጥፋቶች በተሰጠዉ ሥልጣን በላይ መፈጸም ፤

ለ/ ሥራን በተገቢዉ ጥንቃቄ አለማከናወን፤

ሐ/ በሥራ ባልደረባ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጫና ማሳደር፤

**አንቀጽ 15 <u>አድልዎ አለመፈጸም</u>**

**መርህ፡-**ተገልጋዮችን እና የማህበር አባሎችንሁሉ በእኩል ዓይን ማየት እና በሚሰጡ አገልግሎቶች ሁሉ ልዩነት አለመፍጠር፣

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. አድልዎ በሌለበት ሁኔታ ተገቢና ፍትሐዊ በሆነ አኳኋን ዉሳኔ የመስጠትና ሥራቸዉን የማከናወን ግዴታ አለባቸዉ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በጾታ፣በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ወይም አግባብነት በሌለዉ ግምት ምክንያት የተለየ እንክብካቤ ወይም ልዩነት ሳያደርጉ ሥራቸዉን ማከናወን፣
2. ሕግን ብቻ መሠረት በማድረግ መሥራት፣

**በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡**

ሀ/ የአንድን ጉዳይ ፍሬ ነገር/ጭብጥ/መሰረት ያላደረገና አንድን ቡድን ወይምግለሰብ የሚጠቅም ወይም የሚጎዳ አድሎዊ ምክር መስጠት፤

ለ/ ከሕግና ከመመሪያ ዉጭ የሆነ ቅጥር መፈጸም እድገት ሥልጠና ወይም የትምህርት ዕድል መስጠት

**አንቀጽ 16 <u>ሕግን ማክበር</u>**

**መርህ፡-** የሃገሪቱን ሕገመንግስት፣ የማህበሩን መመሪያዎች እና አሰራሮች በማክበር የተሰጠ ን ሥልጣን እና ኃላፊነት በአግባቡ ማከናወን፣

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. ለሕግ መገዛትና ለሥራቸዉ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑ አዋጆችን ደንቦችንና መመሪያዎችን መከተልና ማክበር፣
2. የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ የበላይ ሥራ አመራርና የሥራ መሪዎች በሕጋዊ ሥልጣናቸዉ የሚያስተላልፉትን ትእዛዞች መፈጸም፣
3. የሥራ መሪዎች ሕገወጥ የሆነ ትዕዛዝ ወይም ተገቢ ያልሆነ መመሪያ ወይም ትእዛዝ በሥራቸዉ ላሉ የሥራ መሪዎች ወይም ሠራተኞች ማስተላለፍ፣
4. የበላይ አለቆቻቸዉ የሚሰጡት መመሪያ ወይም ትእዛዝ ሕገወጥ ወይም ተገቢ ካልሆነ መመሪያዉን ወይም ትእዛዙን ለሰጠዉ ኃላፊ ማሳወቅ፣

በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡

ሀ/ የህብረት ስራ ማህበሩን ሕጎችን ወይም የአሠራር ሥርዓቶችን በመጣስ መሥራት ወይም ሕጋዊ የሆኑ ትእዛዞችን አለማክበር ወይም ሌሎች ሠራተኞች እንዲያከብሩ መገፋፋት ወይም ከሕግ ዉጭ እንዲሠሩ መገፋፋት ወይም ማበረታት፤

ለ/ የቅርብ የሥራ ኃላፊዉን ፈቃድ ሳያገኝ ከሥራ መቅረት ፤

ሐ/ መቅረቱ በሥራዉ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስ እያወቀ የቅርብ የሥራ ኃላፊዉን ፈቃድ ሳያገኝ ከአቅም በላይ ባልሆነ ምክንያት ከሥራ መቅረት፤

መ/ ኃላፊዉን መስደብ ወይም መደብደብ ፤

ሠ/ከስራው ጋር በተያያዘ በማንኛዉም ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና በጥፋቱም ምክንያት ለሥራዉ ተገቢ ሆኖ አለመገኘ፤

**አንቀጽ17 <u>ለሕዝብ ጥያቄ ተገቢዉን ምላሽ መስጠት</u>**

**መርህ፡-** አገልግሎት ፈላጊ/ደንበኛ ለሚያነሳቸው/ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች አግባብነት እና ሕግን መሰረት ያደረገ ምላሽ በወቅቱ መስጠት፣

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1. ለባለ ጉዳዮች ተገቢዉን አክብሮት በመስጠትና ትሕትና በማሳየት ለሚቀርብላቸዉ ጥያቄ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ምላሽ መስጠት፣
2. ባለጉዳዮች ግራ ሊጋቡ ትዕግስት ሊያጡና ሊናደዱ ስለሚችሉ የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች በትዕግስት ማስተናገድ፣

በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡

ሀ/ ህዝቡ መብቱን በሚመለከት በምርት /አቅርቦት/ ላይ የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖረዉ ማድረግ ፤

ለ/ ለባለጉዳይ ተገቢዉን ትሕትና አለማሳየት ወይም እገዛ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆን፤

ሐ/ ያለበቂና ሕጋዊ ምክንያት ጉዳዮችን ወይም አቤቱታዎችን ማዘግየት፤

## አንቀጽ 18 አርአያነት

**መርህ፡-በሚሰጡ አገልግሎቶች ለህብረተሰብ እና ለተገልጋይ በሚፈፅሙት ተግባራትና እና በሚታዩ ባህሪያትለሌሎች መልካም ምሳሌ መሆን፣**

ማንኛዉም የሸማች ህብረት ስራ ሠራተኞች እና የሥራ አመራር

1/ ሠራተኞች ሥራ በሚያከናዉኑበት ጊዜና በማህበረሰቡ ዉስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ግንባር ቀደም ምሳሌ በመሆን የሚጠበቅባቸዉን ከፍያለየአርአያነት ጠባይ በማሳየት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መርሆች ማጎልበትና በተግባር እንዲተረጎሙ ማገዝ፣

2/ የኃላፊነት ስሜት የሚሰማቸዉ የተሻለ ለዉጥን የሚደግፉ የባለ ሥልጣኑን መልካም ስም የሚጠብቁና የአሠራር ባህል እንዲዳብር መተማመን ሥር እንዲሰድና ጸንቶ እንዲቆይ የራስን ሚና በብቃት መወጣት፣

በመርሆዉ ሥር የተጠቀሱትን ግዴታዎች በመተላለፍ የሚከተሉትን ጥፋቶች መፈጸም ያስቀጣል ፡፡

ሀ/ ኃላፊነት ያለበት አግባብነት ያለዉን የአሰራርና የስነምግባር መርሆች ለአዲስ ተቀጣሪ ሠራተኞችን አለማሳወቅ፤

ለ/ የሸማች ህብረት ስራ ማህበሩ ተገልጋዮች ወይም ባለጉዳዮችን ወይም የሥራ ባልደረቦችን መዝለፍ ማመናጨቅ ወይም መልካም ስነ ምግባርን በተላበሰ መልኩ አለማስተናገድ ፤

ሐ/ ከኃላፊዎች የኮሚቴ ሥራ እንዲሠራ ትእዛዝ ሲሰጥ ያለበቂ ምክንያት ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆን

# ክፍልሶስት

# የዲሲፕሊን ቅጣት ደረጃዎች እና እርምጃዎች፡-

**አንቀፅ 19 የዲስፕሊን ቅጣትዓላማ፡-**

- የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት ሰራተኞች እና የስራ መሪዎች /ኃላፊዎች ላይ የሚወሰደው የዲሲፒሊን እርምጃዎች ዓላማው በእንዳንዱ መርህ ስር ቅጣት ያስከትላሉ ተብለው የተዘረዘሩትን ተግባራት / ባህሪያት በመፈፀም ጥፋተኛ ሆነው ሲገኙ ተመጣጣኝ ቅጣት በመጣል ከፈፀሙት ጥፋት እንዲታረሙ እና ለወደፊቱ ከጥፋታቸው ታርመው ስራቸውን እና ህይወታቸውን በመልካም ስነምግባር እንዲመሩ ለማድረግ ነው ።
- በሥነ ምግባር የታነጹ ኃላፊና ሠራተኛ ለማፍራት፤
- ኃላፊዎችም ሆኑ ሠራተኞች የሥነ ምግባር ግድፈት እንዳይፈጽሙ ለማስተማርና ፈጽመዉ ሲገኙም በማረም ተገቢ እርምጃ ለመዉሰድ የማይታረም ሆኖ ሲገኝ ከሥራዉ ለማሰናበት ነዉ፡

**አንቀፅ 20 የሚወሰደው የዲሲፒሊን እርምጃዎች አፈፃፀም፡-**

ሀ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በስነምግባር መመሪያ መርሆዎች ውስጥ የሰፈሩትን ሃሳቦች በአግባቡ ባለመፈፀማቸው በፍታብሄር ወይም በወንጀል መጠየቃቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፤የዲሲፒሊን ጉድለት ፈጽመው ሲገኙ፤ በዚህ የስነምግባር መመሪያ በተቀመጡት የዲሲፒሊን ደረጃ ዓይነቶች እርምጃ ይወሰድባቸዋል ፣

ለ ማንኛዉም የዲሲፒሊን እርምጃ አወሳሰድ ከሥራ ማገድ፣ የቅሬታና የይግባኝ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት የሚመራዉ በህብረት ስራ ማህበሩ ሠራተኞች የህብረት ስምምነትና የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይሆናል፡

ሐ. በስነምግባር ግድፈት የሚወሰኑ ቅጣቶች ማንኛውም በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎችን

ሳይጠብቁ ሊፈፀሙ ይችላሉ ፣

መ. ማንኛውንም አመራር፣የስራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ የስነምግባር መመሪያ በእያንዳንዱ የስነምግባር መርህ ስር የሰፈሩትን የስነ ምግባር ግድፈቶች ከፈፀመ በዚሁ መመሪያ በሰፈሩት የቅጣት ደረጃ መሰረት የዲስፕሊን የክስ አመሰራረት፣ አፈፃፀም እና አቀራረብ በአዋጅ 985/2009በሸምግልና በፍታብሔር ወይም በወንጀል ወይም በሁለቱም ሕጎች

ተጠያቂነታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ላደረሱት ጥፋት ወይም የዲሲፕሊን ጉድለት በዚህ የሥነምግባር መመሪያ መሠረት ተገቢዉ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድባቸዋል፡፡

**አንቀፅ 21በመርሆዉ ስር ለተቀመጡት ጥፋቶች የቅጣትደረጃዎች፡-**

በእያንዳንዱ መርሆዎች ስር የተዘረዘሩት/ የተጠቀሱት ጥፋቶች ሲፈጸሙ የዲስፕሊን የክስ አመሰራረት፣ አፈፃፀም እና ቅጣቶች በአዋጅ 985/2009 አንቀጽ64እና65 በተመለከቱት የቅጣት ደረጃዎች መሰረት የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡ የዲሲፕሊን ጥፋቶች በህግ ያስጠይቃሉ፡፡

**በዚህ መሰረት**

**ከላይ የተጠቀሱትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች መተላለፍ በቀላልና ከባድ ዲሲፕሊን ያስቀጣል**

| የሥነ-ምግባር መርሆዎች | በቀላልዲሲፕሊን የሚያስጠይቁ | በከባድ ዲሲፕሊን የሚ ያስጠይቁ |
|---|---|---|
| አንቀጽ 7 ቅንነት | 7/ለ/፣7/መ/፣7/ሠ/፣7/ረ/ | 7/ሀ/፣7/ሐ/ |
| አንቀጽ 8 ታማኝነት | 8/ሀ/፣ 8/መ/ ፣8/ሠ/፣8/ረ/፣8/ቀ/ | 8/ለ/፣8/ሰ/፣8/ሸ/ |
| አንቀጽ 9 ግልጽነት | 9/ለ/፣9/ሐ/ | 9/ሀ/ |
| አንቀጽ 10 ሚስጥር መጠበቅ | 10/ሐ/ | 10/ሀ/፣10/ለ/፣10/መ/ |
| አንቀጽ 11 ሀቀኝነት | - | 11/ሀ/፣11/ለ/ |
| አንቀጽ 12 ተጠያቂነት/ | 12/ሀ/፣12/ሠ/፣12/ረ/ | 12/ለ/፣12/ሐ/፣12/መ/ |
| አንቀጽ 13 የአባላትን ጥቅም ማስቀደም | 13/ሀ/ | 13/ለ/፣13/ሐ/፣13/መ/ |
| አንቀጽ 14 ህጋዊ በሆነ ስልጣን መገልገል | 14/ለ/፣14/ሐ/ | 14/ሀ/ |
| አንቀጽ15አድሎአለመፈጸም | 15/ሀ/ | 15/ለ/ |
| አንቀጽ 16 ህግን ማክበር | 16/ለ/ | 16/ሀ/፣16/ሐ/፣16/መ/፣16/ሠ/ |
| አንቀጽ17ለህዝብጥያቄ ተገቢውን መስጠት | - | 17/ሀ/፣17/ለ/፣/17/ሐ/ |
| አንቀጽ 18 አርአያነት | 18/ሀ/ | 18/ለ/፣18/ሐ/ |

- ቀላል የሥነ ምግባር ግድፈቶችን በተደጋጋሚ ጊዜ መፈጸም ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣትን ያስከትላል፡፡

**አንቀጽ22 የዲሲፕሊን ቅጣት ዓይነቶች**

1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች

ሀ/ የቃል ማስጠንቀቂያ ፣

ለ/ የጹሑፍ ማስጠንቀቂያ፣

ሐ/ በአንድ ጊዜ እስከ አስራ አምስት ቀን የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት፣

2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች፡-

ሀ/ ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ ማድረግ፣

ለ/ ከሥራ ማሰናበት፣

**አንቀጽ 23 የዲሲፕሊን ኮሚቴ ሥለማቋቋም**

የዲሲፕሊን ኮሚቴዉ ሥልጣን በሠራተኞች የህብረት ስምምነትና የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የተቋቋመ ኮሚቴ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ24 የዲስፕሊን ኮሚቴ ስልጣንና አሰራር**

የዲስፕሊን ኮሚቴ ስልጣንና አሰራር በአሰሪና ሰራተኞች አዋጅ መሰረት ይሆናል

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 25 ጥቆማን ስለማሳወቅ

1. ማንኛዉም ሠራተኛ እና ኃላፊ በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተካተቱ መርሆዎችን የሚጻረር የሥነ ምግባር ጉድለት መፈጸሙን በማንኛውም መንገድ ካወቀ ወይም ከተመለከተ ጉዳዩን ለሸማች ማህበሩ አመራሮች ወይም ለአዲስ አበባ ህብረት ስራ ኤጀንሲ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የሚቀርበዉ ጥቆማ እዉነተኛ፣ያልተዛባ፣ ከበቀል የጸዳ፣ አሳሳች ያልሆነና ምክናያታዊ በሆነ እምነት ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ጥቆማ አቅራቢዉ ከማናቸዉም የበቀል ጥቃት የመጠበቅ መብት አለዉ ፡፡
4. ጥቆማ አቅራቢዉ ማንነቱ እንዳይገለጽ ከፈለገ ማንነቱ በምስጢር መያዝ አለበት፡፡

## አንቀጽ 26 የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሠራተኛና ኃላፊ የሥነ ምግባር ክፍሉ ለሥራዉ የሚፈልገዉንና የሚጠይቀዉን መረጃና ድጋፍ በመስጠት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 27 ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን መመሪያ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## አንቀጽ 28 መመሪያዉን ስለማሻሻል

ይህ የሥነ- ምግባር መመሪያ አፈጻጸሙ እየታየ የሚሻሻል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ29 መመሪያዉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ መጋቢት 2010ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**ግዛቸው ዓሊ**

**የአዲስ አበባ ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር**